# የፈተናዎች መመሪያ ለወላጆች

## W-APT (WIDA-ACCESS PLACEMENT TEST)( WIDA-የምደባ ፈተና)

ፈተናዎች ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለትምህርት ባለሙያዎች ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸውን ሚጠበቅበትን እውቀት ስለማወቅ አለማወቃቸው እና ለ 21ኛው መ/ክ/ዘ ዝግጁ ሆነው ለመመረቅ ስለመቻላቸው ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ። እነዚህ የፈተና ውጤቶች በልጅዎ ትምህርታዊ መሻሻል ማስረጃ አካል ውስጥ አንድ ልኬትን ለማቅረብ የታቀዱ ናቸው።

## ይሄ ፈተና ምንድን ነው?

The WIDA-ACCESS Placement Test(  WIDA-ACCESS የምደባ ፈተና  )፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት መለኪያ ፈተና ሲሆን ለአዲስ ተማሪዎች hk-1 ክፍል ላሉ English learners (ELs) (የእንግሊዘኛ ተማሪዎች) ለሆኑ የሚሰጥ ፈተና ነው አስተማሪዉቹ  ELsን ለይተው ለማወቅ እና ፕሮግራም ውስጥ ለመመደብ ያግዛቸዋል። W-APT የማህበረሰብ ቋንቋ እና በትምህርት የሚገኝ ቋንቋን በአራት ክፍሎች በመስማት፣ በንበብ፣ በፅሁፍና በመናገር ይለካል የማህበረሰብ ቋንቋ በየቀኑ ለመግባቢያነት ሲጠቅም፣ በትምህርት የሚገኝ ቋንቋ ክፍል ውስጥ ለመግባቢያነት ይጠቅማል።

## ልጄ የሚፈተነው መቼ ነው?

W-APT ለእንግሊዘኛ ተማሪዎች ከK-1 ወደ ዲስትሪክት (ክፍለ-ከተማ)ው ሲገቡ የሚወስዱትን አንድ ጊዜ የሚሰጥ ፈተና ነው በገቡ በ10 ቀን ውስጥ መመዝገብ ሲችሉ በትምህርቱ አመት ውስጥ በፈለጉት ጊዜ መውሰድ የሚችሉት ፈተና ነው።

## ልጄ ምን ውጤት (ቶች) ይቀበላል?

የመዋለ ህፃናትን መመዘኛ ፈተና የሚስዱ፣ የ1ኛ ክፍል የመጀመሪያ መንፈቀ አመት ተማሪዎችን በማካተት  ለአስተማሪዎች የተማሪዎቹን የእንግሊዘኛ ችሎታ የሚያሳይ መረጃ ነው ኦርጅናሉ(ያልተቀየረው) ውጤት ከተገኘ በኋላ የተማሪው የመጨረስ ችሎታ እና ክህሎት ለማየት ይጠቅማል የመናገር እና የማድመጥ ክፍል ውጤት አንድ ላይ ተጨምቆ፣ ዝቅተኛ ፣ መካከለኛ  ከፍተኛ ወይም የላቀ ተብሎ ደረጃ ይሰጣል።
1 – 12 ክፍል ያሉ ተማሪዎች WIDAን በመጠቀም ይፈተናሉ።

## እነዚህ ነጥቦች ጥቅም ላይ የሚውሉት እንዴት ነው?

ውጤቱም አንድ ተማሪ ድስትሪክቱን ሲገባ ምን ያህል የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ እንዳለው ለማሳየት እንደ መነሻ መረጃ ያገለግላል። ይሄም የእንግሊዘኛ ትምህርት የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየት ይጠቅማል። የአስተማሪዎች ቡድን እና የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎች ይሄንን ውጤት በመጠቀም የትኞቹ ተማሪዎቹ ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ይወስናሉ። ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች ወደ ድስትሪክቱ ሲገቡ  ብቃት ያላቸው ተብለው ሊለዩ ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ

በልጅዎ ትምህርት ውስጥ እንዲሳተፉ እናበረታታዎታለን። እባካችሁ የልጅዎን አስተማሪ በማናገር ልጆችን ቤት ውስጥ እንዴት መርዳት እንዳለባችሁ እና ፈተናውን ለመውሰድ የሚጠቅማቸው ነገሮች እንዲሟላላቸው ለማድረግ ከመጠየቅ ወደኋላ አይበሉ።

**ተጨማሪ መረጃ:- WIDA**

- www.wida.us/assessment/

**ተጨማሪ መረጃ: ፈተናዎች**
ይህን ድረገጽ ይጎብኙ:

- http://assessments.dpsk12.org

ፈተናውዎች ላይ ጥያቄዎች ወይም ስጋት ካለዎ፣ እባክዎ የልጅዎን ት/ቤት በቀጥታ ያናግሩ ወይም የቤተሰብ ተወካይ አገልግሎትን በ (720) 423-3054 ደውለው ያነጋግሩ።